# የህዝቡን ጆሮ በማፈን እውነትን መሸፈን አይቻልም

## በሰሜን አሜሪካ የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች ስብስብ የተሰጠ የጋራ አቋምና መግለጫ

**ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከምርጫ በኋላ አንዳንድ ተቃዋሚዎችን ወደ ፍርድ እናቀርባለን በማለት የሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫና እንዲሁም የአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ የአማርኛ ክፍል ከሩዋንዳ እልቂት ጋር በማመሳሰል ወደ ኢትዮጵያ የሚያደርገውን ስርጭት ሞገዱን እንደሚያፍኑት በይፋ የተናገሩት ንግግር መነሻ በማድረግ የቀረበ አጭር የተቃውሞ መግለጫ እንደሚከተለው ቀርበዋል።**

በመጪው ወርሃ ግንቦት 2002ዓ.ም ይካሄዳል ተብሎ የታሰበው ሀገራዊ ምርጫ ሰላማዊ፣ ፍትሓዊና ሚዛናዊ እንዳይሆን ገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግ በምርጫው ተሳታፊ በሆኑት ተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች ላይ የሚፈፅመው ግድያ፣ አፈና፣ ወከባና ጫና እየተባባሰ መሄዱን በየዕለቱ የሚወጡ የተለያዩ ዘገባዎች ያስረዳሉ። ዛሬ ህዝቡ ብዙ ማስፈራሪያዎችና መሰናክሎችን አልፎ በየስብሰባ ቦታዎች በመገኘት በስርዓቱ ላይ ያለው የከረረ ተዋውሞ በመግለፅ ለለውጥ ያለው ቁርጠኝነት ከቀን ወደ ቀን እያየለ በሄደ ቁጥር ህወሓት/ኢሕአዴግ ራሱ በሚፈጥረው ቀውስ ተዘፍቆ ወደ ተራ የአሸባሪነት ስራ በመሸጋገር በዜጎች ላይ ዓይን ያወጣና ጭካኔ የተሞላበት እርምጃዎች በመውሰድ ላይ ይገኛል።

ባለስልጣናቱም የረገጡት መሬት እየተናደባቸው መሆኑን በመረዳት የሚዙትና የሚጨብጡት በማጣት ፍርሃትና ጭንቀት የወለዳቸው ስድብ፣ ዛቻና ማስፈራሪያ ያዘሉ መግለጫዎች ሲሰጡ እየሰማን ነው። የህዝቡን ነፃ ተሳትፎና የተቃዋሚ ድርጅቶች ነፃ እንቅስወቃሴ የሚገድቡ የተለያዩ አዋጆች ሲደነግጉ በዓይናችን እያየን ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ራሳቸው ዕጩ ተወዳዳሪ ሆነው ሳለ ነገር ግን ራሳቸው ከሕገ መንግስቱ፣ ከምርጫ ቦርዱና ከምርጫ ስነ ምግባሩ ሕግ በላይ በመሆንና የመንግስት ጡንቻ ስልጣናቸው መከታ በማድረግ በሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች ላይ ተደጋጋሚ የስነ ልቦና ጦርነት ሲያውጁ ሰምተናል። ከዚህም አልፈው ከምርጫ በኋላ የተቃዋሚ ድርጅቶች ተወዳዳሪ ዕጩዎችን እንደሚከሱና እንደሚያስሩም በይፋ ተናግረዋል። ይህ በአፀያፊ ስድብና አስደንጋጭ ቃላት እየታጀበ ነጋ ጠባ የሚነሰሙት የጦርነት ነጋሪትና እሱን ተከትሎ እየተወሰዱ ያሉት ሕገ ወጥ እርምጃዎች ዋናው አላማቸው በአንድ በኩል የምርጫውን ሂደት በማደፍረስና አቅጣጫውን በመቀየር የህዝቡን ድምፅ በአቋራጭ ለመንጠቅ የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎች ለማመቻቸት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ህዝቡ በሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች ላይ ጥርጣሬ እንዲያድርበትና ለማደናገር ሲሆን ከሁሉም በላይ ግን በሀገሪቱ ትርጉም ያለውና በአስተማማኝ ህዝባዊ መሰረት ላይ የተገነባ ተቀናቃኝ የፓለቲካ ድርጅት እንዳይፈጠር **የህዝቡን ተስፋ አጨልመው አንገቱን ለማስደፋት** መሆኑን በሚገባ ተገንዝበነዋል።

80 ሚሊዮን ህዝብ የሚመለከት የምርጫ ጉዳይ በአንድ አምባ ገነን ፈላጭ ቆራጭ መሪ እጅ ወድቆ ከሕግ በላይ በመሆን ራሳቸው ዕጩ ተመራጭ፣ ራሳቸው አሳሪ፣ ራሳቸው ፍርድ ሰጪ በመሆን ሀገሪትዋን እንደ ፈለጉ ሲነዱዋትና ሲያተራምሱዋት ማየታችን እጅጉን አሳዝኖናል። በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ኮሚኒስታዊ ስርዓት ስር የተዋቀሩ የፍትሕና የመንግስት አካላትም የዳር ተመልካችና የወር ደመወዝ ጠባቂዎች እንጂ ሕገ መንግስቱንና የህዝቡን ሰብአዊ፣ ዲሞክራሲያዊና ዜግነታዊ መብቶች ሲጠብቁና ሲያስከብሩ አይታዩም። እነዚህ ተቋማት ለአብዮታዊ ዲሞክራሲ ታማኝ የሆነ ሰው ብቻ የሚንከባከቡ እንጂ ሕግን አክብረው በሰላም ለሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ድርጅቶች የሕግ ከለላና የሕግ ዋስትና ሲሰጡ አላየንም። እነዚህ ተቋማት ለኢሕአዴግ መንግስታዊ ልባስ ለመስጠት የተፈጠሩ እንጂ ምርጫው ፍትሓዊ፣ ሚዛናዊ፣ ዲሞክራሲያዊና ተአማኒ እንዲሆን የመቆጣጠር፣ የመፈፀምና የማስፈፀም ዓቅሙም ብቃቱም ፍላጎቱም እምነቱም የሌላቸው፣ በአንድ አምባ ገነን መሪ የሚሽከረከሩ፣ በአንድ ሰው ሳባ የሚተነፍሱ፣ ጥርስ አልባና ህይወት የሌላቸው ጉዑዛን ሆነው ማየታችን እጅጉን አሳዝኖናል።

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በሀገር ውስጥ የነበሩ የግል ጋዜጦች ጠራርገው ከጨረሱ በኋላ ዛሬ ደግሞ ፊታቸው ወደ ውጭ በማዞር ሰሞኑን የአሜሪካ ድምፅ ራድዮ የአማርኛ ክፍል ከሩዋንዳ የዘር እልቂት ጋር በማነፃፀር ክፍሉ ወደ ኢትዮጵያ የሚያደርገው ስርጭት ሞገዱ እንደሚያግዱም በይፋ ገልፀዋል። የአሜሪካ ድምፅ ራድዮ የአማርኛ ክፍል የስርጭቱ ሞገድ ለማፈን የፈለጉበት ዋናው ምክንያት ራድዮው ለኛ ለኢትዮጵያውያን የሩዋንዳን ዓይነት ጥፋት ስለሚመኝልንና ስለሚሰብክ አይደለም። ራድዮው ከህዝቡ ጋር አብሮ ያደገ፣ በህዝቡ ልብ ውስጥ ያለ፣ ህዝቡ ብሶቱን የሚገልፅበት እንደ አንድ አማራጭ መስኮት አድርጎ የሚያየው፣ ለኢትዮጵያ ህዝብ ባለ ውለታው መሆኑን ሁላችንም ጠንቅቀን እናውቃለን። አቶ መለስም ይህንን እውነታ ጠንቅቀው ያውቃሉ የሚል ግምት አለን።

በኛ እይታ በአሁኑ ሰዓት የራድዮውን ስርጭት ሞገድ በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ ህዝብ ጆሮ እንዳይደርስ ያፈኑበትና የከለከሉበት ዋናው ምክንያት “አያ ጅቦ ሳታማኸኝ ብላኝ” ከማለት አልፎ ሌላ ትርጉም የለውም። በምርጫ ወቅት የሚያደርጉትን ማጭበርበርና ከምርጫ በኋላ ይከሰሳሉ በተባሉት አካላት ላይ የሚፈፅሙትን ቅጥ የለሽ ግፍ ዋቢ የሚሆን ዘገባ እንዳይኖር በመፍራት የኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ የውጪውን ዓለም ሓቁን በውል እንዳያውቀው ለመደበቅ ሲባል መሆኑን በሚገባ እንገነዘባዋለን። በመሆኑም እርምጃው 80 ሚሊዮን ህዝብ የሚነካ በተለይም በሀገር ውስጥ የሚኖረው ህዝባችን በቀጥታ መረጃ የማገኘት መብቱን የሚያፍን ከመሆኑም በላይ የራድዮ ጣቢያው የሞያ ነፃነት፣ መብት፣ ክብርና ስም የሚያጎድፍ ስለሆነ አጥብቀን እናወግዛለን። የተደረገው እገዳና የተላለፈው ስም የማጥፋት ዘመቻ መሰረት የሌለው፣ በአልባሌታና በቂም በቀል ላይ የተመሰረተ፣ ለመጪው ትውልድም መጥፎ የታሪክ ጠባሳ ጥሎ የሚያልፍ እርምጃ በመሆኑ በአስቸኳይ እንዲታረም እንጠይቃለን።

በዚሁ አጋጣሚ በአሜሪካ ድምፅ ራድያ ለትግርኛና ለኦሮምኛ ክፍል ዜና አቅራቢዎች ማስተላለፍ የምንፈልገው መልእክትም ከላይ ከተጠቀሰው ነጥብ ብዙም የተለየ ነገር አይደለም። የአቶ መለስ ዜናዊ መንግስት የአማርኛው ክፍል ከትግርኛውና ከኦሮምኛው ክፍል ለብቻው ለይቶ ስርጭቱን ለማገድና ስሙን ለማጥፋት የፈለጉበት ዋናው ምክንያት ቀደም ብለን ከላይ እንደጠቀስነው የክፍሉ ሰራተኞች የህዝቡን ልብ ትርታ እየተከታተሉ ለሀገርና ለወገን የሚጠቅሙ ወቅታዊ ዜናዎችና ጥናታዊ ዘገባዎች በግልፅ በማቅረብ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት በህዝባችን ላይ የሚፈፅማቸውን በደሎች ያለ ማወላወል በዓለም ማሕበረ ሰብ ፊት ስለሚያጋልጡት ነው። ሌላው ምክንያት ደግሞ ስርዓቱ ልክ ሀገር ውስጥ እንደሚያደርገው ሁሉ በተመሳሳይ አንዱን ወዳጅ ሌላውን ጠላት አድርጎ በመፈረጅ እርስ በርስ ለማናከስና በመካከሉ ጥርጣሬ ለመፍጠር መሆኑን ልብ እንድትሉ ይገባል። ስለሆነም እናንተም የክፍላችሁ የዜና ስርዓት መብቱን እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን የምታቀርቡት ዜናም ሆነ ዝግጅት የህዝቡን ብሶትና የሀገር ጉዳይ ማእከል ያደረገ እንዲሆን ስናሳስብ እንዲሁም አቀራረባችሁ ድፍረት፣ ነፃነት፣ ግልፅነት፣ ሚዛናዊነትና ሞያዊ ብቃት የተላበሰ እንዲሆን ከአክብሮት ጋር አደራ እንላለን።

**የተከበራችሁ ውድ ኢትዮጵያውያን!!**

“ሁላችንን በጋራ በእኩልነት የሚዳኝ የሕግ የበላይነት ይከበር። ሁላችን በጋራ የምንጠቀምበት ነፃና ዲሞክራሲያዊ መድረክ ይኑር። የብዙሃኑ መገናኛ ከአንድ ሞኖፓላዊ እጅ ተላቆ የህዝቡ አገልጋይ ይሁን። ህዝቡ መረጃ የማገኘት መብቱን ይከበር። ምርጫው ፍትሓዊ፣ ሚዛናዊ፣ ዲሞክራሲያዊና ተአማኒ እንዲሆን የሕገ መንግስቱንና የምርጫውን ስነ ምግባር ሕጎች ይከበሩ። የዜጎች ሰብአዊ፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶችንና ህሊናዊ እሞነቶችን ይከበሩ። የአመለካከት ልዩነት ይዞ ሕግ አክብሮ በሰላም መንቀሳቀስ የህዝብ መብት እንጂ ጠላትነት አይደለም። በህዝብ መካከል ፍቅር እንጂ ፈፅሞ ጠላትነት የለም። እኛም በሀገራችንና በህዝባችን ጉዳይ ላይ ፍፁም ያገባናል” በማለት በሚጮኹና ጥያቄ በሚያቀርቡ ዜጎች፣ ሓቁን እየተከታተሉ በሚፁፉ ነፃ ጋዜጠኞችና እንዲሁም ምንም ትጥቅ ሳይሆኖራቸው ህዝብንና ሕግን አምነው በሰላም በመንቀሳቀስ ላይ በየሚገኙ ተቃዋሚ ድርጅቶች ላይ ምን ዓይነት ግፍና በደል እየደረሰባቸው እንደሆነ ሚዛናዊ አስተሳሰብና ወገናዊ ሃላፊነት የሚሰማው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉ ልብ ያለው ልብ ይበል እንላለን።

እኛም ህዝባችን መብቱን ለማስከበርና እንዲሁም የስልጣኑን ባለቤት ለመሆን በምርጫው ዙሪያ በሚያደርገው የነቃ ተሳትፎና ሰላማዊ እንቅስቃሴ ሁሉ እየተከታተልን እስከመጨረሻ ከጎኑ በመቆም ዜግነታዊ ድርሻችንን ለመወጣት ዝግጁ መሆናችንን እየገለፅን፣ አምባ ገነኖች ዛሬ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ዓለም በሰለጠነበት ወቅት ስለሀገራችን ጉዳይ እንዳንሰማ ጆሮኣችንን፣ እንዳናይ ዓይናችንን፣ እንዳንናገር አፋችንን ዘግተውና አፍነው በመያዝ እውነትን መሸፈንና ዘላለም ህዝብን ማታለል እንደማይችሉ እንዲያውቁት ይገባል እንላለን።

## ለውጥ የጠማውን ህዝብ በማፈን
## ሓቅን በአደባባይ መሸፈን አይቻልምና።

## በሰሜን አሜሪካ የትግራይ ተወላጆች ስብስብ